በሎስ አንጀለስ የድንግል ማርያም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አመሠራረት ታሪክ

ማሳሰቢያ፦ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የተጠቀሱት ዓመተ ምሕረቶች በአውሮፓውያን የዘመን አቆጣጠር ላይ የተመሠረቱ ናቸው።

ኢትዮጵያውያን በታሪካቸው እንደሚታወቀው ቀደም ባለው ጊዜ ከሀገራቸው ወጥተው በባዕድ አገር መኖር አያሰኛቸውም፣ አይሆንላቸውም ነበር። ሕዝባቸውን ወገናቸውን ሀገራቸውን እጅግ የሚወዱ ናቸው። አልፎ አልፎ ለከፍተኛ ትምህርት ወደ አውሮፓና አሜሪካ ይላኩ የነበሩት ኢትዮጵያውያን የመጡበት ተልዕኮ ተሳክቶ በፍጥነት ወደ ሀገራቸው የሚመለሱበትን ዕለት በከፍተኛ ናፍቆት ነበር የሚጠባበቁት። እንዲያውም አንዳንዶቹ ትምህርታቸውን እንዳጠናቀቁ ሳይውሉ ሳያድሩ ወዲያውኑ ወደ ኢትዮጵያ ስለሚመለሱና በምረቃው ሥነ ሥርዓት ላይም ስለማይገኙ ዲግሪውም ሆነ ዲፕሎማው በፖስታ ነበር ወደ ኢትዮጵያ ከተመረቁበት ዩኒቨርስቲ የሚላክላቸው።
ይሁን እንጂ ከየካቲት 1974 ዓ.ም ጀምሮ በኢትዮጵያ በተፈጠረው የፖለቲካ፣ የማህበራዊና የሌላም ጉዳይ መናጋትና መቃወስ ሳቢያ ከኖረበት ቀዬ እንኳን ወጥቶ ወደሌላ አካበቢ መኖር ጭንቅ የሚሆንበት ኩሩ ኢትዮጵያዊ ሕይወቱን ለማትረፍ ከሚወደው ሕዝብና ሀገሩ ተለይቶ ወደ ባዕድ አገር መሰደድ ግድ ሆኖበታል። በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ሕዝብ በመላው ዓለም ተበትኖ ይታያል። ኢትዮጵያውያን ስደተኞች በብዛት ከሚኖሩባቸው አገሮች አንዱ የዩናይትድ እስቴትስ አሜሪካ ምድር ነው። በዚያ ቀውጢ ቀን የፍቅር እጁን ዘርግቶ የተቀበለን የአሜሪካ መንግሥትና ሕዝብ ታላቅ ባለውለታችን ነው።

የሰው ልጅ የማቴሪያል ወይንም ሥጋዊ ፍላጐቶችን ብቻ በማሟላት ከቶ ረክቶ መኖር አይችልም። በወንጌልም እንደ ተጻፈው ሰው በዳቦ ብቻ መኖር አይችልም። ለመንፈሳዊ ሕይወቱ መንፈሳዊ ፍላጐቶች በአንፃሩ መሟላት ይኖርባቸዋል። ይህ የረጅም ጊዜ የክርስትና እምነት ተከታይ ሕዝብ የትም የት ይኑር በቋንቋውና በባሕሉ ፈጣሪውን የሚያመልክበት ቤተ እግዚአብሔር (ክርስቲያን) ያስፈልገዋል። እንዲሁም የተወለደው ሕፃን ሀብተ መንፈስ ቅዱስን የሚያገኝበት የሥርዓተ ጥምቀት አገልግሎት፣ ሙሽሮች ቃል ኪዳን የሚለዋወጡበት የሥርዓተ ተክሊል አገልግሎት ወዘተ.... ያስፈልጉታል።

ወደዚህ ወደ ሎስ አንጀለስ ለመጡት ለመጀመሪያዎቹ ኢትዮጵያውያን ምእመናን የተጠቀሱትን መንፈሳዊ አገልግሎቶች ማግኘት ቀላል አልነበረም። የነበራቸውም ብቸኛ ምርጫ ወደ ግብፃውያን ቤተ ክርስቲያን መሄድ ነበረ። ምንም እንኳን በሃይማኖት ከግብፅ ኮፕቲክ ቤተ ክርስቲያን ጋር አንድ ብንሆንም ቋንቋው ባሕሉ ሥነ ሥርዓቱ ለኢትዮጵያዊው ምእመን እንግዳ ነገር ነበር።

በሎስ አንጀለስ ከተማ ነዋሪ ለነበሩት ለጊዜው በቁጥር እጅግ አነስተኛ ለነበሩት ኢትዮጵያውያን ምእመናን ለመጀመሪያ ጊዜ የአምልኮተ እግዚአብሔር አገልግሎት መስጠት የተጀመረበት ጊዜ 1979 ዓ.ም ሲሆን አድራሻውም 300 E. 119th St, Los Angeles, CA 90016 ነበር። መንፈሳዊ አገልግሎት መስጫው የተከለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን የሚል ስያሜ ነበረው፤ ሆኖም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት መሠረት የተሟላ መንፈሳዊ አገልግሎት የመስጠት አቅም ገና አልነበረውም። መንፈሳዊ አገልግሎት ይሰጡም የነበሩት ሁለት ኢትዮጵያውያን ያልሆኑ ካህናት ነበሩ። እነዚህ የተጠቀሱት ሁለቱ ካህናት የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዶክትሪንና ሥርዓት በሚችሉት አቅም አጥንተው ከምዕራብ ሀገሮች ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ከአቡነ ይስሐቅ ሥልጣነ ክህነት የተቀበሉ ናቸው። ከሎስ አንጀለስ ታይምስ ጋዜጣ (Los Angeles Times) የቤተ ክርስቲያኗን መቋቋም አንብበው ወደ ተጠቀሰው ሥፍራ ለመጀመሪያ ጊዜ የሄዱት ኢትዮጵያዊ ከቤተ ክርስቲያናችን ነባር አባል አንዱ የዚያን ጊዜው የዩኤስሲ ዩኒቨርስቲ ተማሪ ዶ/ር ሰሎሞን ገብረ ክርስቶስ ነበሩ። በእሳቸውናበሌሎችም አማካኝነት ዜናው በኢትዮጵያውያን ምእመናን ዘንድ ተሰራጨ። በዚህም ጊዜ በቺካጐ የትምህርት ገበታ ላይ ለነበሩት ለሊቀ ሊቃውንት ተክለ ሚካኤል (ነሲቡ) ታፈሰ መጥተው መንፈሳዊ አገልግሎታችውን እንዲያበረክቱ ቤተክርስቲያኗ ጥሪ አቅርባላቸው መጡ።

ቀስ በቀስም የምእመናኑ ቁጥር እየጨመረ መጣ። ቀጥሎም የቤተ ክርስቲያኑን እንቅስቃሴ ለማሳደግና እርዳታም ለማስተባበር ያመች ዘንድ አንድ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ተመሠረተ። ከዚያም በኃላ አንዳንድ ለውጦች ቢደረጉበትም የመጀመሪያውን የመተዳደሪያ ደንብ ረቂቅ የነደፈውም ይህ ኮሜቴ ነበረ። የኮሚቴውም አባላት
የሚከተሉት ምእመናን ነበሩ፦

1. እማሆይ ኢየሩሳሌም ደሕኔ
2. ዶ/ር ተስፋ ወሰኔ
3. ወ/ሮ ፀሐይቱ ገ/ሥላሴ
4. አቶ ጌትነት አለበል
5. ዶ/ር ሰሎሞን ገ/ክርስቶስ

6. ወ/ሮ መሠረት የማነ
7. ወ/ሮ ገነት አድነው
8. አቶ አዳሙ አማረ
9. አቶ ገብረ እግዚአብሔር

መንፈሳዊ አገልግሎቱ ለጥቂት ወራት ከቀጠለ በኋላ በነባሮቹ አሜሪካውያንና ኋላ በመጡት ኢትዮጵያውያን መካከል አንዳንድ አለመግባባትና የሥራ አፈጻጸም ችግሮች ስለተፈጠሩ ኢትዮጵያውያኑ ምእመናን ለቀው ወጡ። ከዚያም ሮበርትሰን ላይ የሚገኘውን የግብፅ ቤተ ክርስቲያን እማሆይ ኢየሩሳሌም ከሊቀ ሊቃውንት ጋር ሆነው በማነጋገር በየሳምንቱ ቅዳሜ እንድንጠቀምበት ተፈቀደልን። ይህም ለመበተን በመቃረብ ላይ ለነበሩት ኢትዮጵያውያን ምእመናን ከፍተኛ ብሥራት ነበረ። ይህም የሆነው በ1980 ዓ.ም ነው።የቤተ ክርስቲያኑም መጠሪያ ስም «ቅድስት ማርያም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን» እንዲሆን የተወሰነው ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ነው። ስያሜውም የመነጨው ከሊቀ ሊቃውንት ተክለ ሚካኤል ነው። እማሆይ ኢየሩሳሌም ደጎኔ ቤተ ክርስቲያኗን ለማስፈቀድ ቀደም ብሎም ካህን ለማግኘት ከአቡነ ይስሐቅ ጋር በመጻጻፍ ያደረጉት ጥረትና ድካም ይህ ነው ተብሎ ለመግለጽ የሚያስቸግር ነው። አቶ ጌትነት አለበልም የጥረቱ ተካፋይ ነበሩ። ሊቀ ሊቃውንትን የሚረዳቸው ተጨመሪ ሌላ ካህን ስላልነበረ በጸሎተ ቅዳሴ ጊዜ አቶ ፍስሐ ገብረ እግዚአብሔር ከመቅደስ ውጭ ሆነው እንደ ዲያቆን ያገለግሉ ነበር።

በዚህን ጊዜ የሚከተሉት አባላት ያሉበት አንድ ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ተመሠረተ፥

1. ሊቀ ሊቃውንት ተ/ሚካኤል (ነሲቡ) ታፈሰ ሊቀ መንበር
2. አቶ አርአያ ጎበዜ ም/ሊቀ መንበር
3. አቶ ዘውዴ ለማ ዋና ጸሐፊ
4. እማሆይ ኢየሩሳሌም ደጎኔ አባል
5. አቶ ጌትነት አለበል አባል
6. አቶ ኃይለ ጊዮርጊስ አስፋው አባል
7. አቶ ፈቃደ ሥላሴ መስፍን አባል
8. ወ/ሮ መንበረ ኃይለ ጊዮርጊስ አባል
9. ወ/ሮ መሠረት የማነ አባል

ኮሚቴው ስብሰባውን ያካሄድ የነበረው ቀደም ሲል በአባላቱ ቤት ኋላም ለሊቀ ሊቃውንት በተከራዩላቸው ቤት ነበር። ግብፃውያኑ የቤተ ክርስቲያኑ ባለቤቶች ጥቃቅን ምክንያቶች በመደርደር በአንድ ወቅት ቤተ ክርስቲያኑን ከመጠቀም አግደዋቸው ነበረ ከልምምጥ በኋላም እንደገናም ተፈቀደላቸው። በሌላ በኩል አገልግሎቱ ከእሑድ ይልቅ ቅዳሜ የመሰጠቱ ጉዳይ የራሱ የሆነ ችግር ነበረው። ከምእመናኑ ለአንዳንዶቹ ቅዳሜ የሥራ ቀን ስለነበረ ለሌሎቹም የግል ጉዳያቸውን የሚያከናውኑበት ዕለት በመሆኑ እመች አልነበረም። በመሐሉም ሊቀ ሊቃውንት ትምህርታቸውን ለመከታተል ወደ ቺካጐ ተመለሱ።

በዚህን ጊዜ የኮሚቴው አባላት በተለይም አቶ አርአያ ጎበዜና እማሆይ ኢየሩሳሌም ተሰፋ ባለ መቁረጥ ካህን ለማግኘት ከአቡነ ይስሐቅና ከሌሎችም ጋር መጻጻፍ ቀጠሉ።የሥራ ምድባቸው ዌስት ኢንዲስ የነበረው በወቅቱ ዕረፍት ላይ የነበሩት አባ ሐዲስ በጊዜያዊነት እንዲያገለግሉ ተደረገ። ወዲያውኑም አባ ኅሩይ የተባሉ ካህን ተተክተው ማገልገል ጀመሩ። በዚያኑ ጊዜ ማለትም በ1981 ዓ.ም ቤተ ክርስቲያኑ ከግብጾቹ በመለየት አድራሻውን በኩክራን ጐዳና በሚገኝ አንድ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በጥገኝነት መሠረተ።

ጥቂት ቆይቶም አባ ወ/ሰማያት አሉላ በስደት ከነበሩበት ሀገር ከሱዳን ቀጥሎም መምህር መንግሥቱ ንጉሤ ከኢየሩሳሌም በመምጣት ለተፈጠረው የካህን እጥረት መፍትሔ አስገኙ (እነዚህ ሁለት አበው ካህናት እስካሁንም ለመላው የሎስ አንጀለስ የኦርቶዶክስ ምእመናን ከሃያ ዓመታት በላይ በቅንነትና በትጋት በማገልገል ላይ ይገኛሉ። የተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ከተቋረጠ በኋላም ቀሲስ አማረ መንግሥቱ በፈቃደኝነት መጥተው ከሁለቱ ካህናት ጋር አብረው አገልግለዋል። ከዕለት ወደ ዕለት የምእመናን ቁጥር እየጨመረ መጣ። በዚያውኑ መጠን ምእመናኑ በቤተ ክርስቲያን የወደፊት እድገት ያላቸው ተስፋና አለኝታ መጠቀ። ክብረ በዓል ሳይኖር በተራው የሰንበት (የእሑድ) ቀን ከሙዳየ በረከት እስከ አምስት ሺህ ዶላር ወይንም ከዚያ በላይ የተሰበሰበበት ጊዜ ነበረ። ምንም እንኳን እያንዳንዱ ምእመን ቤተ ክርስቲያኗን ለማጠናከር የከፈለው መሥዋዕትነት በቀላሉ የማይታይ ቢሆንም እዚህ ላይ ሊጠቀስ የሚገባው በተለይ ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት አቶ አርአያ ጎበዜ የደከሙት ድካም ያበረከቱትም አስተዋጽዖ ምንም ጊዜም የማይዘነጋ መሆኑ ነው።

ከዚህም ቀጥሎ በካሊፎርኒያ ስቴት ለመጀመሪያ ጊዜ በሕግ ታውቆ የተመዘገበው የአመራር ቦርድ በምእመናን ተመርጦ ተቋቋመ። አባላቱም የሚከተሉት ነበሩ፥

1. አቶ ፍስሐ ገ/እግዚአብሔር ሊቀ መንበር
2. አቶ ተፈራ ኃይሌ ም. ሊቀ መንበር
3. አቶ ሞገስ ሽፈራው ዋና ጸሐፊ
4. ወ/ሮ የኔወርቅ አለማየሁ አባል
5. አቶ ሐዲስ ሐጎስ አባል
6. ወ/ሮ የምሥራች አግዴ አባል
7. ወ/ሮ ማርታ ነጋሽ አባል
8. አቶ ሰይፉ መኮንን አባል

ይህ ቦርድ አስተዋይነትና ትእግስት በተሞላበት የአመራር ችሎታና ሰልት በቤተ ክርስቲያኑዋ ታሪክ ውስጥ እጅግ አስቸጋሪ የነበሩትን መሰናክሎችና የፈተና ወቅቶች ከምእመናኑ ጋር ያሳለፈ ነው። ምእመናኑን በማስተባበርም ለመጀመሪያ ጊዜ ቤተ ክርስቲያኑዋ የራስዋ የሆነ ሕንጻ ባለቤት እንድትሆን ያበቃት ነው። በአጠቃላይም በቤተ ክርስቲያኗ የእድገት ታሪክ ውስጥ ይህ ቦርድ ከፍተኛ ድርሻ የሚሰጠው ነው።

እንዲሁም ከነባር አባላት መካከል ዶ/ር ጌታቸው መካሻ፣ አቶ ዘውዴ ለማ፣ አቶ ይልማ ዳኘ፣ ዶ/ር ሃጎስ ኃብተዝጊ፣ አቶ መርዕድ ማንያዘዋል ሌሎችም ስማቸው ያልተጠቀሰ አባላት የቤተ ክርስቲያንዋን ደንብ ባሻሻለ ኮሚቴ፣ ባስመራጭ ኮሚቴ፣ ባዛውንት ኮሚቴ ወዘተ በአጠቃላይም የቤተ ክርስቲያኑዋን እድገትም ሆነ ችግር በሚመለከቱ ጉዳዮች ሁሉ በተለያዩ ጊዜያት በቅንነት አገልግለዋል። እያገለገሉም ነው፥ በተለያዩ ምክንያቶች በአሁኑ ጊዜ ከኛ ጋር የሌሉ እንደነ ሲስተር ፋንታዬ አሻግሬ የመሳሰሉት ለቤተ ክርስቲያናችን እድገት አስተዋጽኦ አድርገዋል።

ነዋሪነታቸው እና መደበኛ አገልግሎት የሚሰጡበት ኒውዮርክ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ቢሆንም አባ ጳውሎስ በእንግድነት እየተጋበዙ አልፎ አልፎ ሎስ አንጀለስ በመምጣት ለምእመናኑ መንፈሳዊ አገልግሎት ይሰጡ ነበረ። ለቤተ ክርስቲያኗ የወደፊት እድገት ምእመናኑን በማስተባበር በተለይም ወንጌልን በማስተማር ይረዱናል በሚል እምነት የአባ ጳውሎስ አገልግሎት ሰፋ ባለ ሁኔታ ይቀጥል የሚል ሀሳብ ካንዳንድ ምእመናን መጣ ሆኖም ጉዳዩ በተለያዩ ምክንያቶች ወዲያውኑ ከፍተኛ ተቃውሞ አስከተለ። ከዚያም «አባ ጳውሎስ እየመጡ ያገልግሉ» እና «አይምጡብን» በሚሉት ሁለት ፍጹም ተቃራኒ ሐሳቦች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ ለመስጠት ያመራር ቦርዱ የአባል ምእመናን ጠቅላላ ጉባኤ ጠራ። የቤተ ክርስቲያኗን የወደፊት እድገት ለማየት በከፍተኛ ተስፋ ላይ ለነበሩት ምእመናን ጉዳዩ ቀላል ፈተና አልነበረም። እንደተፈራውም በቤተ ክርስቲያኗ ታሪክ ውስጥ አሳዛኝ ሁኔታ ተፈጠረ። በቀረቡት በሁለቱ የውሳኔ ሐሳቦች ውጤት ምክንያት ቤተ ክርስቲያኗ ከሁለት ተከፈለች። አንደኛዋ «ቅድስት ማርያም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን» የሚለውን መጠሪያ እንደያዘች ያለችዋ ስትሆን ሁለተኛዋ መከፈሉ እንደተከሠተ «ቅድስት ማርያም የኢትዮጵያ ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን» በአሁኑ ጊዜ ግን «ድንግል ማርያም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን» በመባል የምትታወቀዋ ናት። ከዚህ በታች የሚከተለው ጽሑፍ የሚያተኩረው ድንግል ማርያም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ላይ ይሆናል።

ከመከፋፈሉም በኋላ «ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ» የሚለውን ሐረግ መጠቀምን በሚመለከት ጉዳይ ሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት ለዓመታት በፍርድ ቤት ተሟግተዋል። ከሁለቱም ወገን ለጠበቃ ከፍተኛ ወጪ ተደርጓል። የጠበቃ ወጪን በሚመለከት የቤተ ክርስቲያኗ የገንዘብ አቅም በጠበቆቹ ግምት ለጊዜው አስተማማኝ ሆኖ ባለመገኘቱ በሥራ አስኪያጁ ቦርድ ውስጥ በወቅቱ አመራር ላይ የነበሩት አቶ ፍስሓ ገብረ እግዚአብሔር (ሊቀመንበር) እና አቶ ተፈራ (ም. ሊቀመንበር) እንዲሁም የገንዘብ አስተዋጽዎ ንዑስ ኮሚቴ ሊቀመንበር ወ/ሮ ዕፀገነት መካሻ የግል ንብረታቸውንና ክሬዲት ካርዶቻቸውን በቤተ ክርስቲያኗ ስም ዋስትና አስይዘዋል።

ለመሆኑ ለዚያ ሁሉ አለመግባባትና ከእንደዚያ ዓይነት አስከፊ ደረጃ ላይ ለመድረስ ትክክለኛ መንሥኤው ምን ነበረ ወይንም ማን ነበረ የሚለውን ጥያቄ ለጊዜው ወደ ጐን እንተወዋለን። ይሁን እንጂ ጥሩው ዜና ያ ለዘመናት ተጋርጦ የቆየው ያለመግባባት ግርዶሽ ተወግዶ በአሁኑ ጊዜ በሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት መካከል ሰፍኖ የሚታየው መፈቃቀር መደጋገፍ፣ መተሳሰብ እጅግ የሚያስደስት መሆኑ ነው። ከምእመናኑ ቁጥር ብዛት የተነሳ ተግባራዊ ለማድረግ ስለሚያስቸግር ካልሆነ በቀር የሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት ምእመናን ተጠቃልለው በአንድ ቦታ በአንድ የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ የማይገለገሉበት ምንም ምክንያት የለም። ይህን ለማየት ይህን ለመመስከር ያበቃንን ከሃሊና የፍቅር አምላክ እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን።

ከመከፋፈሉ ቀጥሎ በድንግል ማርያም ቤተ ክርስቲያን የተከሠተው ችግር የካህናትና የሰባክያን ማጣት ጉዳይ ነበር። ችግሩንም ለጊዜው ለመቋቋም ከምእመናኑ መካከል መጠነኛ የመንፈሳዊ ትምህርት የነበራቸው ተራ ገብተው በየሳምንቱ አሐድ ትምህርት እንዲያቀርቡ ተደረገ። ይህ በእንዲህ እንዳለ ለሕክምና ከኢትዮጵያ መጥተው የነበሩ አባ ኪሮስ

የሚባሉ ካህን እንዲሁም በስደት ከሱዳን ምድር መጥቶ እዚህ ይኖር የነበረው አፈወርቅ በዲቁና በጊዜያዊነት ማገልገል ጀመሩ። ሁለቱ ካህናት ከለቀቁ በኋላ፥ መምህር ገብረ ሥላሴ ከግብጽ ገዳም፣ ቀሲስ ተስፋዬ አያሌው (የዚያን ጊዜው ዲያቆን ተስፋዬ)፥ እንዲሁም አባ ኢሳይያስ (በአሁን ጊዜ የአክሱም ሊቀ ጳጳስ) እና ቀሲስ ሙሴ በመምጣት አገልግሎታቸውን ቀጠሉ።

መምህር ገብረ ሥላሴና ቀሲስ ተስፋዬ ያለ ረዳት ካህን ብቻቸውን ለአንዲትም ሰንበት ቅዳሴ ሳይታጎል ረዘም ላለ ጊዜ አገልግለዋል። በተለይም መምህር ገብረ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያኗ በከፍተኛ ፈተና በተወጠረችበት ወቅት ለምእመናኑ አባታዊ ምክር በመለገስ መረጋጋት እንዲሰፍን ታላቅ አስተዋጽዖ አድርገዋል። በዚህም መሠረት ካህን የማግኘቱ ችግር ውሎ አድሮ መፍትሔ አገኘ። በዚህን ጊዜ ሁሉ መንፈሳዊ አገልግሎቱ ይካሄድ የነበረት ቦታ በተለያዩ ጊዜ ለተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት መጠነኛ ወርኃዊ ኪራይ ከፍለን በጥገኝነት በመኖር ነበር። በውላችን መሠረት ባለንብረቶቹ በማይጠቀሙበት ሰዓት ማለትም ዘወትር እሑድ እስከ አራት ሰዓት (10፡00AM) የጸሎተ ቅዳሴውንና ሌላውንም ተጨማሪ አገልግሎታችንን አጠናቀን በአስቸኳይ ሥፍራውን አጽድተን ለባለቤቶቹ መልቀቅ ነበረብን። በነበረውም ጥድፊያ ምክንያት ብዙውን ጊዜ ለዕለቱ በመርሐ ግብሩ ከታቀዱት ወስጥ አንዳንዶቹን መሰረዝ ግድ ነበር። ከሥርዓቱ ፍጻሜ በኋላ በነበረው አጭር የቁርስ ሰዓትን በሚመለከትም እንዲሁ ተመሳሳይ ችግር ነበር። የቆረቡትን ሳይበሉ መውጣት የተለመደ ነበር። ዘወትር ቅዳሜ ለእሑድ አጥቢያ ከሰዓት በኋላ ከምእመናን አንዱ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ በመሄድ መጋረጃውንና ሌሎችንም አስፈላጊ ዝግጅቶች ያከናውናል። ዓላማውም፣ ሥርዓቱ የሀገራችን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ይዘት እንዲኖረው ነው። ንዋያተ ቅድሳቱ በከፊል ይቀመጡ የነበረው በካህናቱ መኖሪያ ቤት ነበረ። ምንም ያህል ከፍተኛ ጥንቃቄ ቢደረግም አንዳንድ ጊዜ አገልግሎቱ ሊጀመር ጥቂት ደቂቃ ሲቀ ረው አንድ ተረስቶ ሳይመጣ የቀረ ነገር ይኖራል። ይህም ሁኔታ ችግሮችን ይፈጥር ነበር።

ያስጠጉን ባለንብረቶች በጥቃቅን ምክንያቶች እንድንለቅ ማስጠንቀቂያ ይሰጡን ነበር። ያስወጡንም ጊዜ አለ። በእኛም በኩል አልፎ አልፎ ስህተት ይደረግ ነበር። ይህም ሁኔታ ለምእመናኑ ስለሚቀርበው መንፈሳዊ አገልግሎት የረጅም ጊዜ እቅድ ለማውጣትና ንብረትም ለማፍራት አላስቻለም። እርግጥ የችግሩ ዘለቄታዊ መፍትሔ የራስ መገልገያ ቤተ ክርስቲያን መግዛት ነበረ። ይሁን እንጂ ይህን ተግባራዊ ለማድረግ በወቅቱ ችግሮች ነበሩ። የምእመናኑ ቁጥር ከማነሱ በተጨማሪ አብዛኞቹ በዝቅተኛ ገቢ የሚተዳደሩ ነበሩ። ከባንክ ለቤተ ክርስቲያን ሕንፃ መግዣ የገንዘብ ብድር ለማግኘት ደግሞ ቤተ ክርስቲያኗ ከዚሁ ቀደም ተበድራ ያላንዳች ችግር የከፈለች እንደነበረች የሚያሳይ የክሬዲት ዘገባ (CREDIT HISTORY) ማስረጃ አልነበረም። በተጨማሪም በኢትዮጵያውያን ማኅበረሰብም ሆነ አብያተ ክርስቲያናት አካባቢ በተደጋጋሚ የተከሠተው የመከፋፈልና የመለያየት ጉዳይ አንዳንዶች ምእመናን ተስፋ እንዲቆርጡና በኅብረትና በአንድነት አሠራር ላይ አመኔታ እንዲያጡ ስላደረገ በመጠኑ የተሻለ ገቢ የነበራቸው ጥቂቶች ምእመናን ቢኖሩም የልግስና እጆቻቸውን ከመዘርጋት እንዲቆጠቡ አድርጓቸዋል። ለቤተ ክርስቲያኗ ገቢ ለማስገኘት በተደረገው የማያቋርጥ ጥረት በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ ዝግጅቶችና ፕሮግራሞች በሎስ አንጀለስ ከተማና አካባቢዋ ለሚገኙ ነዋሪዎች እንዲቀርቡ ተደርገዋል።

ከብዙ ጥረትና ትግል በኋላ ከሠላሳ የማይበልጡ ምእመናን በግንቦት ወር 1989 በወ/ሮ ዘነበች እሸቱ ና ባለቤታቸው አቶ ሰሎሞን መኖሪያ ቤት በመሰብሰብ ለቤተ ክርስቲያን ሕንፃ መግዣ መነሻ የሚሆን በድምሩ $38,000 ዶላር ለማዋጣት እያንዳንዳቸው ቃል ገቡ። ከዚያም የገንዘብ አስተዋጽዖውን ሥራ በሰፊው የሚያስተባብር በወ/ሮ ዕፀ ገነት መካሻ የሚመራ በሥራ አስኪያጅ ቦርድ ሥር አንድ ኮሚቴ ተመሠረተ። ለሕንፃውም መግዣ ቋሚ ወርሃዊ የገንዘብ አስተዋጽዖ ለማድረግ ምእመናኑ ቃል የሚገቡበት ቅጽ እንዲሞሉ ተደረገ። በዚህም መሠረት ክፍያው ከሐምሌ 1991 ዓ.ም ተጀመረ። ይህ ኮሚቴ የተጣለበትን ኃላፊነት ለመወጣት በከፍተኛ ትጋት የቅስቀሳውን ሥራ ቀጠለ። ምእመናኑም ተባባሪነታቸውን በተግባር አስመሰከሩ። ሥራ ያላቸው ገንዘባቸውን፣ ገቢ የሌላቸው የአንገታቸውን ወርቅ የጣታቸውን ቀለበት፣ የጆሮአቸውን ጉትቻ አበረከቱ። ይሁን እንጂ ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው ያለበቂ ዋስትና በመጠነኛ ወለድ የሚያበድር ፈቃደኛ ባንክ ለማግኘት አልተቻለም። የአመራር ቦርዱ ለችግሩ ዘለቄታዊ መፍትሔ ለማግኘት ጥረቱን ያለተሰፋ መቁረጥ ቀጠለ። በዚህም መሠረት ጁላይ 15 ቀን 1991 ዓ.ም (በ 4544 S.Compton Ave. የሚገኘውን) አሁን የምንገለገልበት የቤተ ክርስቲያን ሕንፃ ከባንክ በከፍተኛ ወለድ በተገኘ ብድር በ$495,000 ዶላር ተገዛ። ይህ ታላቅ የቤተ ክርስቲያኗ የታሪክ ዓምድ ነበር። እንደ እግዚአብሔር ፈቃድም በሰሜን አሜሪካ ምድር በራሳቸው የቤተ ክርስቲያን ሕንፃ ለመገልገል ምእመናኑን የመጀመሪያዎቹ አድርጓቸዋል። የአዋሽ፣ የመሶብ የመርካቶ የሮዝሊን ምግብ ቤቶች የሰላም ገበያ እና ሲ. ኤንድ ኬ የግሪክ መደብር በዚያ የችግር ጊዜ ላቀረብንላቸው የእርዳታ ጥያቄዎች ሁሉ ተባባሪዎቻችን ስለነበሩ በዚህ አጋጣሚ ልናመሰግናቸው እንወዳለን።

ከላይ የተጠቀሰው ሕንፃ በቅርጹና በይዘቱ የሀገራችንን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን እንዲያንፀባርቅ በማሰብ መጠነኛ መስተካከል ከተደረገለት በኋላ ከነሐሴ 1991 ዓ.ም ጀምሮ በአገልግሎት ላይ ውሎ ይገኛል። መቅደሱን በማሻሻል መድኃኔ ዓለም እኅትማማቾች የጽዋ ማኅበርና አቶ ነጸረ፤ እንዲሁም ቅጥር ግቢውን አስፋልት በማልበስ አቶ ኤልያስ መሸሻ ወጪውን ሸፍነዋል። በዚህም ለዘመናት ምእመናኑን ሲያሳስብና ሲያስጨንቅ የነበረው ከቦታ ወደ

ቦታ የመንከራተትና የመጣበብ ችግር በእግዚአብሔር ፈቃድ መፍትሔ አግኝቷል። መንፈሳዊ አገልግሎቱም አደገ። ብዙ ሳይቆይ እስከዚያን ጊዜ ያልነበረ በቤተ ክርስቲያኗ እና በአባ ጳውሎስ መካከል አለመግባባት ተፈጠረ ወዲያውኑም አባ ጳውሎስ ለሹመት ወደ ኢትዮጵያ ሄዱ። ቀጥሎም በአባ ጳውሎስና በቤተ ክርስቲያኗ መካከል ከተፈጠረው አለመግባባት ጋር በተያያዘ ምክንያት ከምእመናኑ አንድ ቡድን ከአንድ ካህን ጋር በመገንጠል ለብቻው ሌላ ቤተ ክርስቲያን መሠረተ (ይህም የተገነጠለው ክፍል ብዙ ሳይቆይ እንደገና ከሶስት ቤተ ክርስቲያን ተከፍሏል)።

በመደጋገም የተከሰተው ድርጊት ያሳዘናቸውና ያስቆጣቸው አንዳንድ ምእመናን በፈቃዳቸው ከቤተ ክርስቲያኗ ተለዩ። በቤተ ክርስቲያኗ እድገትና አንድነት ላይ ሠፍኖ የነበረውን ብሩህ ተስፋ አጠያያቂ አደረገው። የእያንዳዱ ምእመን ከቤተ ክርስቲያን መገለል ማለት ከዚያ ምእመን ይሰበሰብ የነበረው ወርኀዊ የአባልነትና የሕንፃ መዋጮ በዚያኑ መጠን ይቀንሳል ማለት ነው። አዲስ ለገዛነው ሕንፃ በየወሩ መከፈል ያለበት የባንክ እዳ አፍጥጦ እየመጣ ነው። ውጥረቱ ቀላል አልነበረም። ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው ባበዳሪ ባንኮች ዘንድ ስለ ቤተ ክርስቲያናችን የመክፈል አቅም የተሰጠው ግምገማ እጅግ ዝቅተኛ ስለነበረ በገባነው ውል መሠረት ወለዱም ሆነ ወርኀዊ ክፍያው ቀላል አልነበረም። በተጨማሪም እስከ ሐምሌ ወር 1994 ዓ.ም ድረስ በአንድ ጊዜ መከፈል ያለበት $110,000 ክፍያ ግዴታ (BALOON PAYMENT) ነበረብን።

የመጀመሪያውን ቦርድ የተካው ሁለተኛው ቦርድ ወዲያውኑ ጠቅላላ ጉባኤ በመጥራት በተለይም የባንኩን ብድርና ክፍያ በማስመልከት የጉዳዩን አሳሳቢነት አስረዳ በተጨማሪም ይበጃል ብሎ የሚያምንበትን አመራጭ መፍትሔ ለጠቅላላው ጉባኤ አቀረበ። የቀረበው አማራጭ መፍትሔ ከሌላ ባንክ የተሻለ ውል ለመደራደር የሚያስችል አስቸኳይ ልዩ መዋጮ ምእመናኑ እንዲያደርጉ የሚጠይቅ ነበረ። ጠቅላላው ጉባኤ ሐሳቡን በሙሉ ድምፅ ደገፈው። እንደታቀደውም ከሌላ ባንክ በመጠነኛ ወለድ በመደራደርና አስፈላጊውን የገንዘብ ብድርም በማግኘት ከፊተኛው ባንክ ቤተ ክርስቲያኗ የሚፈለግባት ዕዳ በሙሉ ተከፈለ። ሂሳቡ ተዘጋ ከዚያም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ነገሮች እንደገና ቀስ በቀስ ጥሩ አቅጣጫና መስመር መያዝ ጀመሩ።

ለሥራ አፈጻጸምና ቅልጥፍና እንዲያመች በአመራሩ ቦርድ ሥር የተደራጁት የልዩ ልዩ መንፈሳዊ አገልግሎት ንኡሳን ኮሚቴዎች በተለይም የትምህርት ኮሚቴ፣ ሃይማኖተ አበው የወጣቶች የሰንበት ት/ቤት ኮሚቴ፣ የሕዝብ ግንኙነትና ማኅበራዊ ጉዳይ ኮሚቴ ከምንጊዜውም ይበልጥ በመጠናከር ከፍተኛ እንቅስቃሴ አድርገዋል።

በቤተ ክርስቲያኗ የወንጌል አገልግሎት ታሪክ ውስጥ ሊጠቀስ የሚገባው የወጣቱ ሐዋርያ የአባ ወልደ ትንሣኤ አያልነህ በዚያ ወቅት በአሜሪካ ምድር በተለይም ቤተ ክርስቲናችን በተቆረቆረችበት በሎስ አንጀለስ ከተማ እንደ ንጋት ኮከብ ብቅ ማለት ነው። መምህሩ ከእግዚአብሔር ባገኙት ልዩ የማስተማር ተውኅቦ የአሜሪካንን ምድር አነቃንቀውታል። አገልግሎታቸው በሎስ አንጀለስ ከተማ ብቻ ሳይወሰን በመላው የአሜሪካ ምድር በካናዳና በመጠኑም በሀገራችን በኢትዮጵያ ጭምር ተዳርሷል። በአገልግሎቱም ጥራትና ስፋት መጠን በአጭር ጊዜ ውስጥ የምእመናኑ ቁጥር በአራት እጥፍ ከማደጉ በላይ እያንዳንዱ ምእመን ስለ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ሥርዓት አጥጋቢ ዕውቀት ለማግኘት በቅቷል።

በተለያዩ ጊዜያት በነበሩት የትምህርት ኮሚቴዎችም አማካይነት በአባ ወልደ ትንሣኤ የሚሰጠው የወንጌል አገልግሎት በእቅድ ተዘጋጅቶ ሥልጣኔ ባስገኘው የትምህርት ማሰራጫ ዘዴዎች ሁሉ በሰፊው ተናኝቷል።

መጽሐፍ ቅዱስን (የአማርኛውን ቅጅ) በብዛት ከኢትዮጵያ በማስመጣትና ለምእመናኑ እንዲዳረስ በማድረግ ቀደም ባለው ጊዜ ይታይ የነበረው እጥረት እንዲወገድ ሆኗል። የምእመናንን ተሳትፎ ለማሳደግም የቅዳሴ ተሰጥዎ፣ ልዩ ልዩ ያሬዳዊ ዜማዎች፣ እንዲሁም የአማርኛ መዝሙሮች በትንሽ መጽሐፍ መልክ ተዘጋጅተው ለምእመናኑ በአገልግሎት ላይ እንዲውሉ ተደርጓል።

ተተኪውን ትውልድ በማዘጋጀት ረገድ ወጣቶቹን በሰንበት ትምህርት ቤት በማደራጀት አስፈላጊውን ትምህርት ቤተ ክርስቲያኗ በመስጠት ላይ ትገኛለች። በተጨማሪም እዚህ የተወለዱት ሕፃናት የሀገራቸውን ቋንቋ፣ ፊደል፣ ሃይማኖት ታሪክ፣ ባሕል ... ወዘተ እንዲማሩ ጥረት እየተደረገ ነው።

ቀደም ባለው ጊዜ በተለያዩ ምክንያቶች ወደተለያዩ እምነቶች የኰበለሉባትን ልጆቿን ቤተ ክርስቲያኗ ቀስ በቀስ በማሰባሰብ ላይ ትገኛለች። ለዚህም ተልእኰ በተለይ አባ ወልደ ትንሣኤ ያደረጉት አስተዋጽዖ እጅግ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ነው።

የሂሳብ መግለጫዎችና የቤተ ክርስቲያኗን እንቅስቃሴ እድገትና ተጨባጭ ሁኔታዎች የሚገልጹ ሪፖርቶች እጅግ ዘመናዊ በሆነ አሠራር ለምእመናኑ በየወቅቱ እንዲቀርቡ ተደርጓል።

ቤተ ክርስቲያናችን ገና በመቋቋም ላይ ይገኙ ለነበሩ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት የራሷን ካህናትና ሰባክያን ረዘም ላለ ጊዜ በመላክ የበኩሏን እርዳታ አበርክታለች። ለማስረጃም የሳን ዲዬጐ ቅዱስ ገብርኤልን፣ የላስ ቬጋስ ቅዱስ ሚካኤልን እንዲሁም የካናዳን አብያተ ክርስቲያናት መጥቀስ ይቻላል።

በማኅበራዊ ጉዳይም ኢትዮጵያውያንን በማቀራረብና እንዲሁም ለከፋውና ሆድ ለባሰው አጋርና የሀገር ናፍቆት መወጫ በመሆን አቅሟ የሚፈቅደውን ሁሉ በማድረግ ላይ ትገኛለች። እዚህ ላይ ሳንጠቅስ ማለፍ የማንፈልገው ቁም ነገር ከሀገሩ ከኢትዮጵያ ውጭ የሚኖር ኢትዮጵያዊ ሁሉ ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚሄደው እንደ ሀገራችን ለአምልኮተ እግዚአብሔር ብቻ ያለመሆኑን ነው። ተቀዳሚውና ዐቢዩ ዓላማ አምልኰተ እግዚአብሔር ቢሆንም በተመሳሳይ መንገድ የሀገሩን የወገኑን የባሕሉን ናፍቆት ለመወጣትም ጭምር ነው። ስለዚህም ነው በእምነት ረገድ እኛን የማይመስሉን የሀገራችን ልጆች በኢትዮጵያዊነት ብቻ አልፎ አልፎ በቤተ ክርስቲያናችን ክብረ በዓል ላይ በመካከላችን የሚገኙት።

እዚህ ላይ በተጨማሪም ልንጠቅሰው የምንወደው ላለፉት ዓመታት ቤተ ክርስቲያናችን ላበረከተችው መንፈሳዊ አገልግሎት ታላቅ ብርታት የሆኑትን ብፁዓን አባቶች ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅንና ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስን ነው ። ብፁዓን አባቶቻችን በጸሎታቸውና በአባታዊ ቡራኬያቸው በበዓላት ላይ እየተገኙ በሐዋርያዊ ተልእኳቸው ምእመናንን የሚጎበኙና ሁልጊዜ በአባታዊ ምክራቸው በሃይማኖት እንዲጸኑ የሚያደርጉ ናቸው። እነዚህን ብፁዓን አባቶች በዚህ በስደት ዓለም የሰጠን ልዑል እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን ።